የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETA

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

አስራ አራተኛ ዓመት ቁጥር ፳፮
አዲስ አበባ-ሚያዝያ ፲፮ ቀን ፳፻

በኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

14th Year No.26
ADDIS ABABA-24th April, 2008

## ማውጫ

ደንብ ቁጥር ፻፵፰/፳፻
የመከላከያ ኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ድርጅት ማቋቋሚያ ደንብ ................................ ገጽ ፬ሺ፷፩

## CONTENTS

Regulation No. 148 /2008
Defence Construction and Engineering Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation. …. Page 4061

**የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፵፰/፳፻**

**የመከላከያ ኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ድርጅትን ለማቋቋም የወጣ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ**

የሚኒስትሮች ምክር ቤት የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ አስፈጻሚ አካላትን ሥልጣንና ተግባር ለመወሰን በወጣው አዋጅ ቁጥር ፬፻፸፩/፲፱፻፺፰ አንቀጽ ፭ እና በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/፲፱፻፹፬ አንቀጽ ፵፯ (፩) (ሀ) መሠረት ይህን ደንብ አውጥቷል፡፡

፩. አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ "የመከላከያ ኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ድርጅት ማቋቋሚያ የሚኒስትሮች ምክር ቤት ደንብ ቁጥር ፻፵፰/፳፻" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

፪. መቋቋም

፩. የመከላከያ ኮንስትራክሽንና ኢንጂነሪንግ ድርጅት (ከዚህ በኋላ "ድርጅት" እየተባለ የሚጠራ) የመንግሥት የልማት ድርጅት ሆኖ በዚህ ደንብ ተቋቁሟል ፡፡

፪. ድርጅቱ በመንግሥት የልማት ድርጅቶች አዋጅ ቁጥር ፳፭/ ፲፱፻፹፬ መሠረት ይተዳደራል ፡፡

፫. ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን

የድርጅቱ ተቆጣጣሪ ባለሥልጣን የሀገር መከላከያ ሚኒስቴር ይሆናል ፡፡

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION No. 148/2008**

**COUNCIL OF MINISTERS REGULATION TO PROVIDE FOR THE ESTABLISHMENT OF DEFENCE CONSTRUCTION AND ENGINEERING ENTERPRISE**

This Regulation is issued by the Council of Ministers pursuant to Article 5 of the Definition of Powers and Duties of the Executive Organs of the Federal Democratic Republic of Ethiopia Proclamation No. 471/2005 and Article 47 (1) (a) of the Public Enterprise Proclamation No. 25/1992.

1. *Short Title*

This Regulation may be cited as the "Defence Construction and Engineering Enterprise Establishment Council of Ministers Regulation No. 148/2008".

2. *Establishment*

1) The Defence Construction and Engineering Enterprise (hereinafter the "Enterprise") is hereby established as public enterprise.

2) The Enterprise shall be governed by the Public Enterprises Proclamation No. 25/1992.

3. *Supervising Authority*

The Ministry of National Defence shall be the supervising authority of the Enterprise .

፬. <u>ዋና መሥሪያ ቤት</u>

የድርጅቱ ዋና መሥሪያ ቤት በአዲስ አበባ ሆኖ ቅርንጫፍ መሥሪያ ቤቶች እንደአስፈላጊነቱ በማናቸውም ሥፍራ ሊኖረው ይችላል ::

፭. <u>ዓላማ</u>

ድርጅቱ የተቋቋመባቸው ዓላማዎች የሚከተሉት ናቸው፤

፩. በዋነኛነት የሀገሪቱ የመከላከያን ግንባታ ፍላጎት ለማሟላት ማንኛውንም የኮንስትራክሽን ሥራ መሥራት፣

፪. በተጓዳኝ የመንገድ ፣ የግድብ ፣ የመስኖ፣ የሕንጻና ሌሎች የኮንስትራክሽን ሥራዎችን መሥራት እና ፣

፫. ዓላማዎቹን ከግብ ለማድረስ የሚረዱ ማናቸውንም ሌላ የንግድ ሥራ መሥራት::

፮. <u>ካፒታል</u>

ለድርጅቱ የተፈቀደው ካፒታል ብር ፬፻ ሚሊዮን ብር (አራት መቶ ሚሊዮን ብር) ሲሆን ከዚህ ውስጥ ብር ፩፻፸፩ሚሊዮን ፬፻፹፬ሺ.ህ ፯፻፷፭ከ፵፬ ሳንቲም (አንድ መቶ ሰባ አንድ ሚሊዮን አራት መቶ ሰማንያ አራት ሺ.ህ ሰባት መቶ ስድሳ አምስት ብር ከአርባ አራት ሳንቲም) በጥሬ ገንዘብና በዓይነት ተከፍሏል ::

፯. <u>ኃላፊነት</u>

ድርጅቱ ካለው ጠቅላላ ንብረት በላይ በዕዳ ተጠያቂ አይሆንም ::

፰. <u>ድርጅቱ የሚቆይበት ጊዜ</u>

ድርጅቱ ላልተወሰነ ጊዜ ይቆያል ::

፱. <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በፌዴራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የጸና ይሆናል ::

አዲስ አበባ ሚያዚያ ፲፮ ቀን ፪ሺ.ህ ዓ.ም.

መለስ ዜናዊ

የኢትዮጵያ ፌዴራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

ጠቅላይ ሚኒስትር

4. *Head Office*

The Enterprise shall have its head office in Addis Ababa, and may have branch offices elsewhere, as may be necessary.

5. *Purposes*

The purposes for which the Enterprise is established are :

1) To engage in any construction activity mainly to satisfy the national defence construction needs;

2) In parallel, to engage in the construction of roads, dams, irrigation infrastructures, buildings and other construction works; and

3) To engage any other business conductive to the attainment of its purposes.

6. *Capital*

The authorized capital of the Enterprise shall be Birr 400,000,000 (four hundred million birr) of which birr 171,484,765.44 (one hundred seventy one million four hundred eighty four thousand seven hundred sixty five birr and forty four cents) is paid up in cash and in kind.

7. *Liability*

The Enterprise shall not be liable beyond its total assets.

8. *Duration*

The Enterprise is established for an indefinite duration.

9. *Effective Date*

This Regulation shall enter into force up on the date of publication in the Federal Negarit Gazeta.

Done at Addis Ababa, this 24th day of April, 2008

MELES ZENAWI

PRIME MINISTER OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIIOPIA